# ወደ ዲጂታል ቴሌቪዥን (DTV) የመለወጫው ጊዜ መጣ፡፡

***ለዕጹብ ድንቅ ቴሌቪዥን ይዘጋጁ፡፡***

**በህጉ መሰረት፣ በጠቅላላ ሀገሪቱ የሚገኙ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች**
ከፌብሪዋሪ 17 ቀን 2009 ጀምሮ ስርጭቶቻቸውን ከአናሎግ ወደ ዲጂታል መለወጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ከኬብል፣ ከሳተላይት፣ ወይም ከስልክ ኩባንያ የቴሌቪዥን አገልግሎት ጋር የተገናኙ ቴሌቪዥኖች ምንም ችግር የማይገጥማቸው ሲሆን ከለውጡ ቀን በኋላም ፕሮግሞችን መቀበላቸውን ይቀጥላሉ፡፡ ነገር ግን ሲግናላቸውን ከአንቴና የሚቀበሉና ከሚከፈልበት የቴሌቪዥን አገልግሎት ጋር ያልተገናኙ አናሎግ ቴሌቪዥኖች፣ ከለውጡ ቀን በኋላ የቴሌቪዥን ስርጭትን ለመቀበል ይችሉ ዘንድ የሃምሚ ተርጓሚ/ለዋጭ ሳጥን ያስፈልጋቸዋል፡፡

## ዲጂታል ቴሌቪዥን (DTV) ምንድን ነው?

**ዲጂታል ቴሌቪዥን (DTV) ከፍተኛ የፈጠራ ውጤት የሆነ ስዕሎችን ልክ እንደኮምፒዩተር በአየር ሞገድ አማካኝነት በዳታ ባይትስ የሚያስተላልፍ አዲስ የስርጭት/የብሮድካስት ቴክኖሎጂ ነው፡፡** DTV **የቲቪ ጣቢያዎች በአስደናቂ ሁኔታ ጥርት ያሉ ስዕሎችን፣ የበለጠ የድምጽ ጥራትን፣ እና በርካታ የፕሮግራም አማራጮችን እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል፡፡**

**እንደዚሁም** DTV **የ**(HD) **ቴሌቪዥን ያላቸው ተመልካቾችም ከፍተኛ ጥራትና ግልጽነት ያለው** (HD) **ስርጭትን ለመከታተል እንዲቻላቸው ያደርጋል፣ እናም መስተጋብራዊ ችሎታን እና በከፍተኛ መጠን ብርታት ያለው የዝግ ካፕሺንና የዳታ አገልግሎቶችን የመሳሰሉትን ያቀርባል፡፡**

## ለውጡ ለምን አስፈለገ?

**በኮንግረስ በተላለፈው ህግ መሰረት**
**– የእጥረት ቅነሳ ድንጋጌ** 2005 **– ባለ ሙሉ ኃይል የአካባቢ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የአናሎግ የስርጭት መስመራቸውን በፌብሪዋሪ** 17, 2009 **ላይ መዝጋት እንዳለባቸውና ስርጭታቸውንም በተለዩ በዲጂታል አቅርቦት እንዲቀጥሉ ይጠበቅባቸዋል፡፡**

## የDTV ጥቅሞች ምንድን ናቸው?

**DTV ለብሮድካስቲንግ በጣም ውጤታማው መንገድ ነው፣ እንደዚሁም የአየር ሞገዱን ለተለያዩ አዳዲስ አገልግሎቶች ነጻ ያደርጋል፡፡ እንደዚሁም ደግሞ፣** DTV **ኩልል ብለው**

**የጠሩ ስዕሎችንና ድምጽን ይሰጣል፤ ተጨማሪ መስመሮችና እንዲያውም ነጻ በአየር-ላይ ከፍተኛ ጥራትና ግልጽነት ያለው ቴሌቪዥን** (HDTV) **ለተጠቃሚዎች ከ** HD **የቴሌቪዥን ሴት ጋር ያቀርባል።**

DTV **እንደዚሁም ከበፊቱ በጣም በበለጠ ሁኔታ ከነጻ የብሮድካስት ቴሌቪዥን ጋር በርካታ አገልግሎቶች እንዲቻሉ ይፈቅዳል።**

## ተጠቃሚው ማን ነው?

**ነጻ የብሮድካስት ቴሌቪዥን ሲግናልሎች በቴሌቪዥኖች ላይ ከተገጠሙ ባለአናሎግ ቲዩነር አንቴናዎች የሚቀበሉ ደንበኞች – እና ከኬብል፤ ከሳተላይት ወይም ከቴሌፎን ኩባንያ የቴሌቪዥን አገልግሎት አቅራቢ ጋር የግዢ ውል ያልገቡ – በዚህ የሽግግር ወቅት ሊቸገሩ ይችላሉ።**

**ቢያንስ 19.6 ሚሊዮን ቤተሰቦች በቤታቸው ውስጥ በተለየ ሁኔታ ነጻ የቴሌቪዥን ስርጪት/ብሮድካስት ያገኛሉ፤ እንደዚሁም ደግሞ በግምት** 70 **ሚሊዮን የቴሌቪዥን መቀበያዎች ከፌብሪዋሪ** 17 2009 **ጀምሮ ከባለሙሉ-ኃይል የቴሌቪዥን ጣቢያ ይቀበሉ የነበሩትን ሲግናል የማጣት ሁኔታ ይደቀንባቸዋል፤ የነዚህ የቴሌቪዥን መቀበያ ባለቤቶች ለማሻሻል እርምጃ ካልወሰዱ በስተቀር።**

## ወደ DTV እንዴት አድርጌ ማሻሻል እችላለሁ?

**በፌብሪዋሪ 17, 2009 ላይ ከሚከተሉት ሶስቱ እርምጃዎች አንዱን በመከተል ወደ DTV ማሻሻል ይችላሉ፡**

**1. DTV ለዋጭ ስጥን፡** አሁን ባለው የቴለሌቪዥን መቀበያዎ ላይ የሚገጠም DTV ሳጥን ይግዙ። ለዋጭ ሳጥኑ ነጻ የቴሌቪዥን ስርጭት እንዲቀበሉ ያስችልዎታል፤ ሳጥኖቹም፤ በግምት በ$40 እና በ$70 ዶላር መካከል የሚሆን ዋጋ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በ2008 መጀመሪያ አካባቢ ላይ በገበያ ላይ ይውላሉ። የፌዴራሉ መንግስት እነዚህን ሳጥኖች ለመግዛት የሚያስችል የ$40 ዶላር ዋጋ ያለው ኩፖን እየሰጠ ነው።
*(See below for details)*
(ለዝርዝሩ ዝቅ ብለው ይመልከቱ)

**2. ዲጂታል ቲቪ መቀበያ፡** በሲስተሙ ውስጥ ዲጂታል የተገጠመለት ወይም የላቀ የቴሌቪዥን ሲስተምስ ኮሚቴ (ATSC) ቲዩነር (ጣቢያ ፈላጊ) ያለበት፤ ከ$100 በታች በሆነ ዋጋ የሚጀምረውን አዲስ ቴሌቪዥን ይግዙ። ዲጂታል ቲዩነር ያላቸው ቲቪዎች ሁሉ በቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሚተላለፉትን ዲጂታል ሲግናሎችን ለመቀብል ስለሚችሉ ያለመንም ወርሃዊ ክፍያ ነጻ ፕሮግራምዎን ማግኘትዎን መቀጠል ይችላሉ።

**3. የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች፡** የአናሎግ ቲቪዎን መጠቀም ለመቀጠል ከፈለጉና፤ ሁሉም ተፈላጊ የአካባቢ ስርጪቶች በዚያ ኩባንያ የተያዙ ከሆነ፤ ከኬብል፤ ከሳተላይት ወይም ከቴሌፎን ኩባንያ አገልግሎት አቅራቢ አገልግሎቱን ይዘዙ።

## DTV ለዋጭ ሳጥን መንድን ነው?

**DTV ለዋጭ ሳጥን ከአናሎግ ቴሌቪዥንዎና አንቴናዎ ላይ የሚሰካና የዲጂታል ቴሌቪዥን ሲግናልን ወደ አናሎግ በመለወጥ ሲግናሉ በአናሎግ ቲቪ ላይ እንዲታይ የሚያደርግ**

**ኤሌክትሮኒካዊ** መሳሪያ ነው። የለዋጭ ሳጥኖቹ ዋጋ በ$40 እና $70 ዶላር መካከል እንደሚሆን ይጠበቃል።

## ለDTV ለዋጭ ሳጥን ኩፖን ማግኘት የምችለው እንዴት ነው?

**ወደ ዲጂታል ለማሻሻል የሚያስፈልገውን ወጪ ለማገዝ፣ የፌዴራሉ መንግስት የ** DTV **ለዋጭ ሳጥኖች ኩፖን እየሰጠ ነው።** ቤተሰቦች፣ ለእያንዳንዳቸው $40 ዶላር የሚያወጡና፣ በ90 ቀናት ውስጥ መወሰድ ያለባቸው እስከ ሁለት ኩፖኖች መጠየቅ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ ወይም ኩፖኑን ለመጠየቅ፣ 1 (888) DTV-2009 ወይም 1 (877) 530-2634 ይደውሉ። (TTY)፣ www.DTV2009.gov ይጎብኙ ውይም የኩፖን ማመልከቻዎን በመ.ሣ.ቁ PO Box 2000, Portland, ወይም 97208 ይላኩ።

## አናሎግ ቲቪዬን እንዳለ ማቆየት እችላለሁ?

**አዎ። አዲስ ዲጂታል ቴሌቪዢን መግዛት** የDTV ስርጭትን ለመከታተል ብቸኛው አማራጭ አይደለም። የአናሎግ ቲቪዎን መጠቀምዎን መቀጠል ከፈለጉ፣ ወደ ዲጂታል ቴሌቪዢን ለማዛወር ቀጥሎ የተመለከቱትን አማራጮች ከግምት ማስገባት ይኖርብዎታል፡
1. የDTV ለአናሎግ ቴሌቪዢኖች አዲስ የዲጂታል ሲግናሎችን ወደ አናሎግ ስልት የሚገለብጠውን ለዋጭ ሳጥን ይግዙ።
2. አዲሱን የዲጂታል ሲግናል ለመቀበል ይቻልዎት ዘንድ፣ ከኬብል፣ ከሳተላይት ወይም ከቴሌፎን ኩባንያ አገልግሎት አቅራቢ ጋር የግዢ ውል ይዋዋሉ።

## ያለኝ ቲቪ አናሎግ ወይ ዲጂታል መሆኑን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

**ቲቪዎ** ከአየር-ላይ-የሚቀለብ ዲጂታላዊ ስርጭት/ብሮድካስት ሲግናልን የሚቀበል መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የባለንብረቱ መመሪያ የሚለውን ማኑዋል ይመልከቱ፣ ወይም የላቀ የቴሌቪዢን ሲስተምስ ኮሚቴ (ATSC) ቲዩነር (ጣቢያ ፈላጊ) ያለበት መሆኑን ይመልከቱ። እንደዚሁም ደግሞ ከእቃው ሰሪ ፋብሪካ ድረ-ገጽ ላይ በመሄድና በፈብራኪው ሞደል ቁጥር አኳያ የቴሌቪዢኑን የአቅም መጠን መመልከት ይችላሉ።

## HDTV ከ DTV ጋር ተመሳሳይ ነው እንዴ?

**አይደለም። DTV ዲጂታል ቴሌቪዢን ነው። HDTV** ከፍተኛ ጥራትና ግልጽነት ያለው ቴሌቪዢን ነው። HDTV ከፍተኛው የDTV የጥራት ደረጃ ይዘት ሲሆን፣ ይህ ግን ከበርካታዎቹ ይዘቶቹ አንዱ ብቻ ነው። ባለከፍተኛ ጥራትና ግልጽነት ቴሌቪዢን ያላቸው ተጠቃሚዎች፣ አንቴናን በመጠቀም ከፍተኛ ጥራትና ግልጽነት ያላቸው የቴሌቪዢን ፕሮግራሞችን በነጻ ሊቀበሉ ይችላሉ።

## DTVን ከአየር ላይ ለመቀበል እችል ዘንድ ልዩ/ስፔሺያል አንቴና ይስፈልገኛል እንዴ?

**ጥሩ የቤት ውስጥ ወይም የውጪ አንቴና** የDTVዎን አቀባበል የላቀ ለማድረግ በቂ ነው። ባጠቃላይ፣ አስተማማኝ የDTV አቀባበል እንዲኖር ከተፈለገ በወቅቱ በቤትዎ ውስጥ ላለው የአናሎግ ቲቪ ሲግናል መቀበያነት እየተገለገሉበት ያለው ተመሳሳይ አንቴና ዓይነት ያስፈልጋል። የአካባቢ ቲቪ ስርጭት/ብሮድካስት መስመርን በነጻ ለማግኘት

**የሚያስችልዎትን የውጭ እንቴና ለመምረጥ እንዲችሉ እርዳታ ከፈልጉ፤ ይህን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡**
www.antennaweb.org.

**በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ከ8,300 በላይ የሚሆኑ ነጻ፣ አካባቢያዊ የሬዲዮና የቴሌቪዢን ጣቢያዎችና ብሮድካስተሮች መረብ ባካተተው የብሄራዊ ብሮድካስተሮች ማህበር አማካኝነት የቀረበ ሀሳብ።**
**ፌብሪዋሪ** 17, 2009

(Continued on back page)
*( በጀርባው ይቀጥላል)*

- *Low-power and class A TV stations are exempt.

*ባለአነስተኛ-ሃይል እና ደረጃ A ጣቢያዎች ከዚህ ነጻ ናቸው።